# የዲሲ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ላይ ክስ እንዴት እንደሚመሰረት?

ከተወሰኑ የዲሲ ኤጀንሲዎች ውሳኔ ላይ የማይስማሙ ከሆነ፣ **ክስዎ እንዲሰማ የዲሲ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶች ጋር የመጠየቅ መብት አለዎት።** *(ቀጣዩ ገጽ ላይ ይግባኝ ሊጠይቁባቸው የሚችሏቸው ኤጀንሲዎችን ዝርዝር ይመልከቱ።)* የይግባኝ ጥያቄዎን በ 4 ቅደም ተከተሎች ማቅረብ ይችላሉ።



## ቅደም ተከተል 1፡- “በድጋሚ ይታይ ጥያቄ” ቅጽን ይሙሉ።

ይሄ ቅጽ ለመሙላት ፈጣን ነው። ትክክለኛውን ቅጽ ለማግኘት፣ የይግባኝ ፍርድ ቤቶችን (202) 879-2700 ላይ ይደውሉ ***ወይም*** ቅጹን ኦንላይን ለመሙላት ቅደም ተከተሎችን ይከተሉ፡-

- ወደዚህ ይሂዱ https://www.dccourts.gov/services/forms/።
- ገጹ ጫፍ አቅራቢያ(ሰማያዊው የፍለጋ አዝራር አጠገብ)፣ ተሳቢ የምርጫ አዝራሩን ለ “ምድብዎን ይምረጡ” (“Choose Your Category”)ላይ ይጫኑ እና “የይግባኝ ፍርድ ቤቶች” (“Court of Appeals”) ላይ ይጫኑ።
- “**በድጋሚ ይታይ ጥያቄ**” (“Petition for Review”) የሚለውን ቅጽ ይፈልጉ።




## ቅደም ተከተል 2፡- ይግባኙን እና ይግባኝ የሚጠይቁበትን የውሳኔውን ቅጂ ያስገቡ።

ቅጹን ከሞሉ በኋላ፣ ከእነዚህ መንገዶች ውስጥ (ከትዕዛዙ ወይም ዓባሪ ከተደረገው ውሳኔ ጋር) ከእነዚህ መንገዶች መሰረት **በአንደኛው** ያስገቡት፡-

- ሰነዶቹን ወደዚህ **ኢሜይል** ያድርጉ efilehelp@dcappeals.gov።
- የፍርድ ቤቱ **የመዝገብ ቤት** ላይ በአካል በመምጣት ቅጂውን **ያምጡት።** አድራሻው ይሄ ነው 430 E Street NW, Washington DC 20001። ፍርድ ቤቱ ከሰኞ እስከ አርብ ከጠዋቱ 8:30 AM እስከ ከሰዓት 5:00 PM ድረስ ክፍት ነው(ሕጋዊ ከሆኑ የበዓል ቀናት በስተቀር)።
- ከላይ የተጠቀሰው አድራሻ ላይ ለፍርድ ቤቱ ቅጂውን **በደብዳቤ** ያላኩ ***ይሄ አማራጭ አይመከርም።***




## ቅደም ተከተል 3፡- የማስሞያ ክፍያውን ይክፈሉ(የክፍያ ማስነሻ የሌሎት ከሆነ)

የክፍያ ገንዘቡ $100 ዶላር ነው። ይሄንን ክፍያ መክፈል የማይችሉ ከሆነ፣ የክፍያ ማስነሻ የሚጠይቁበትን ቅጽ ያቅርቡ። የክፍያ ማስነሻ ቅጽን እዚህ ላይ ያግኙ https://www.dccourts.gov/sites/default/files/2017-06/dcca_form7a.pdf። በድጋሚ ይታይ ጥያቄ በሞሉበት ተመሳሳይ መንገድ ይሄንን ቅጽ በተመሳሳይ ጊዜ ላይ ያስገቡ።



## ቅደም ተከተል 4፡- ለሁሉም ወገኖች በድጋሚ ይታይ ጥያቄውን በደብዳቤ ይላኩ።

***እገዛ ይፈልጋሉ?*** *(202) 628-1161 ላይ ሌጋል ኤድ ጋር ይደውሉ ወይም ወደዚህ ይሂዱ www.legalaiddc.org/online-intake/።*

የእርስዎን የይግባኝ ጥያቄ (ከትዕዛዙ ወይም ከውሳኔው ጋር ዓባሪ በማድረግ) ቅጂዎችን ለሌላኛው ተከሳሽ/ከሳሽ ወገን ወይም ለጠበቃቸው ይላኩ። *አድራሻቸው ይግባኝ የሚጠይቁበት ትዕዛዝ ወይም ውሳኔ ጋር ከተያያዘው የአገልግሎት ምስክር ወረቀት ላይ አለ።*

## በድጋሚ ይታይ ጥያቄ ለማስገባት የመጨረሻ የጊዜ ገደብ አለ?

አዎ። ውሳኔውን በ **ደብዳቤ** ያገኙ ከሆነ፣ "የአገልግሎት ምስክር ወረቀት" ላይ ከተጠቀሰው የደብዳቤ መላኪያ ቀን ጀምሮ **35 ቀናት** አሎት። ውሳኔውን በሌላ መንገድ ያገኙ ከሆነ፣ ይግባኝ ለመጠየቅ **30 ቀናት** አሎት። የእርስዎን ይግባኝ ጥያቄ በደብዳቤ የላኩ ከሆነ፣ ፍርድ ቤቱ ***እስከሚቀበለው*** ድረስ ፋይል አይደረግም። በዚህም የተነሳ ነው በደብዳቤ መላክ የማናበረታታው።

## ቀጥሎ ምን ይፈጠራል?

ፋይል ካስገቡ በኋላ፣ ፍርድ ቤቱ የእርስዎ ክስ መዝገብ ላይ ያሉትን ቀጣይ ሂደቶች ላይ ፍርድ ቤቱ ትዕዛዝ ይሰጣል። በተለምዶ፣ ስለተከሰተው ነገር መዝገብ እንዲያቀርቡ ለኤጀንሲው 60 ቀናት ይሰጣል። ጥያቄዎች ያለዎት ከሆነ፣ የይግባኝ ሰሚ ፍርድ ቤቶችን በ **(202) 879-2700** ላይ ደውለው ያግኙ።

* በዚህ መመሪያ የሚሸፈኑ የዲሲ ኤጀንሲዎች የሚያካትቱት (ይሄ የከፊል ዝርዝር ነው):-

- የአስተዳደር ሰሚ ችሎት ቢሮ
- የቤቶች ባለስልጣን
- የአልኮል መጠጥ ቁጥጥር ቢሮ
- የካሣ ግምገማ ቦርድ (የሠራተኞች ካሣ)
- የክራይ መኪናዎች መመሪያ (ታክሲ መኪናዎች)
- የፖሊስ እና እሳት አደጋዎች የጡረታ እና ማገገሚያ ቦርድ
- የክራይ ቤቶች ኮሚሽን
- የውሃ እና ፍሳሽ ባለስልጣን
- የዞን ኮሚሽን